# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**ተዛማጅ ሠነዶች፦** ACG-RB, COA-RB, IGO-RA, IJA, IJA-RA, IKC-RA, IOE-RA, IOI-RA, JEA RA, JEE-RA, JHC, JHC-RA

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦** Office of the Chief Academic Officer; Office of the Chief of Human Resources and Development

## በቤት እና በሆስፒታል ማስተማር

I. **አላማ**

በሜሪላንድ ህግ መሠረት፥ በአካል ወይም በስሜታዊ የጤንነት እክል ምክንያት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ድረስ ሄደው መማር የማይችሉ ተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በቤት እና በሆስፒታል ትምህርት (HHT) የሚሰጥበትን ሒደት ለመደንገግ ነው።

II. **ዳራ**

በቤት እና በሆስፒታል ማስተማር (HHT) ማለት፦ በአካል ወይም በስሜታዊ የጤና እክል ምክንያት ወደ ትምህርት ቤታቸው እየሄዱ መማር ለማይችሉ ተማሪዎች ዋና ዋና ትምህርት የሚሰጥበት የአጭር ጊዜ አገልግሎት ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) HHT አገልግሎት እንዲሰጥ የሚወስነው የአካል ወይም ስሜታዊ የጤና ሁኔታ እክል ሲኖር እና ሁኔታው ተማሪው(ዋ) HHT ላይ እንዲሳተፍ/እንድትሣተፍ በሚያስገድድ ሁኔታ ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተማሪው(ዋ) HHT አገልግሎት እንዲያገኝ/እንድታገኝ ይወሰናል።

በቤት እና በሆስፒታል ማስተማር (HH) ግቡ ተማሪው(ዋ) በተቻለ ፍጥነት ወደ መደበኛ ትምህርታዊ ፕሮግራም እንዲመለስ/እንድትመለስ ማመቻቸት ነው። HHT በተለይ የሚሰጠው የአካል ወይም የስሜታዊ ጤንነት እክል ሲያጋጥም ሕክምና በመውሰድ ላይ በመሆናቸው ምክንያት በሳምንት ከተወሰኑ ሰአታት በላይ ት/ቤት መከታተል ለማይችሉ ተማሪዎች የሚሰጥ አገልግሎት ነው። HHT---

A. አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም አይደለም።

B. የተማሪዎችን አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም ለመተካት የታለመ ወይም የተነደፈ እቅድ አይደለም፣ እና

C. ፐብሊክ ስኩል ያልሆነ ልዩ ትምህርት ቤት ውስጥ ምደባን ለሚጠብቁ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወይም የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ ለሚያደርጉ ተማሪዎች እንደ ጊዜያዊ ምደባ ሊያገለግል አይችልም።

HHT የተማሪ ህክምና እቅድ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፣ነገር ግን የትምህርት ቤቱ ትኩረት መሆን ያለበት ተማሪው(ዋ) በተቻለ ፍጥነት ወደ ትምህርት ቤት የሚመለስበትን እቅድ የሚደግፍ መሆን አለበት።

**III. ትርጉም**

A. ለ HHT አላማ ኀልማሳየሚባለው፡- ትምህርት በሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ የተማሪው(ዋ)ን ሃላፊነት የሚወስድ እድሜ 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ነው።

B. ለዚህ ደንብ ዓላማ ፍቃድ ያለው/ያላት የጤና አገልግሎት ሰጪማለት፡- –

1. አካላዊ የጤና እክል መኖሩ የተረጋገጠ ተማሪን ሁኔታ በሚመለከት፣ ፈቃድ ያለው/ያላት የህክምና ዶክተር ወይም ሰርተፊኬት ያለው/ያላት ነርስ ፕራክቲሽነር/ባለሙያ፣ ወይም

2. የስሜታዊ ጤንነት ችግር ያለበ(ባ)ትን ተማሪ ሁኔታ በሚመለከት ፈቃድ ያለው (ያላት) የስነ-ልቦና ባለሙያ፣ፈቃድ ያለው (ያላት) የስነ-አእምሮ ሐኪም፣ የአእምሮ ጤና ባለሙያ ነርስ ወይም የሙያ ሠርተፊኬት ያለው (ያላት) የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስት ነው/ናት።

C. ለትምህርታዊ ውሳኔ አሰጣጥ ዓላማ ብቁ የሆነ(ች) ተማሪማለት፡- ዕድሜው(ዋ) 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ(ች) ወይም ከቤተሰብ ኃላፊነት ነጻ የሆነ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

D. HHT ኬዝ ማኔጀር HHT ለሚሰጣቸው ተማሪዎች አገልግሎቶችን የሚያስተባብር/የምታስተባብር MCPS - HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ማለት ነው። ይህ(ች) ሰው እንደአግባቡ ከተማሪው(ዋ) የትምህርት ቤት ካውንስለር እና የተማሪ ግላዊ የትምህርት እቅድ (IEP) ቡድን አባላት ጋር በመቀናጀት ለእያንዳንዱ ተማሪ የማስተማር አገልግሎቶችን ያስተባብራል/ታስተባብራለች እና ይከታተላል/ትከታተላለች። የብቃት ሁኔታ ከተረጋገጠ በኋላ የተማሪዎች፣የወላጆች/የአሳዳጊዎች እና የትምህርት ቤት ግንኙነትን በሚመለከት በዋናነት ኃላፊነት የሚመለከተው HHT አስተዳዳሪን/ተወካይን ነው።

E. ለዚህ ደንብ ዓላማየተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤትማለት፡- የተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ወይም MCPS ደንብ JEE-RA፣የተማሪ ዝውውር እና አስተዳደራዊ ምደባመሠረት የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ነው።

**IV. የአሠራር ቅደምተከተል**

A. የብቁነት መስፈርት

1. HHT ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የሚሰጠው --

a) ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ተመዝግበው ለሚማሩ፣ ወይም የሕዝብ ባልሆነ ትምህርት ቤት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለተመደቡ፣ እና

b) በተረጋገጠ የአካል ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ምክንያት ተማሪ ቢያንስ ለአራት ሳምንታት ለሚቆይ ጊዜ ትምህርት ቤት ለመከታተል አለመቻል፤ወይም በተቆራረጠ ጊዜ ከትምህርት ቤት የሚያስቀር አካላዊ ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ሲያጋጥም ነው።

2. የተረጋገጠ የአካል ጤንነት እክል ሲያጋጥም ብቻ በቤት እና በሆስፒታል ትምህርት እንዲሰጥ የሚቀርብ የተሞላ MCPS ቅጽ 311-15B፣ ማመልከቻ፣ወይም በስሜታዊ የጤና እክል ምክንያት ሲያጋጥም ብቻ MCPS ቅጽ 311-15C፣በቤት እና በሆስፒታል ትምህርት እንዲሰጥ የቀረበ ማመልከቻ፣ ብቁ የሚያደርግ መሆኑን ወይም አለመሆኑን HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ HHT ከመጀመሩ በፊት ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት።

3. የሚከተሉት ተጨማሪ ምክንያቶች ሊካተቱ ይችላሉ፡-

a) ከወሊድ በኋላ፣የወለደች አራስ ተማሪ ቢያንስ ለስድስት ሳምንታት HHT ትምህርት ለማግኘት ብቁ ልትሆን ትችላለች። (እርጉዝ እና የወለዱ ተማሪዎችን ትምህርት እንዲቀጥሉ ስለመርዳት የሚደነግግ MCPS ደንብ IOE-RA፣እርጉዝ እና የወለዱ ተማሪዎችን ትምህርት መቀጠል የሚያስችላቸው መመሪያ ይመልከቱ።) ብቁ የሚያደርጋቸው የአካል ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ያላቸው እርጉዝ ወይም የወለዱ ተማሪዎች ከሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ጋር የተመጣጠነ HHT ትምህርት ሊሰጣቸው ይችላል።

b) ተማሪ በጊዜያዊነት ከትምህርት ቤት እንዲቀር/እንድትቀር በሚያስገድድ የአካላዊ ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ምክንያት ተማሪዎች HHT እና በት/ቤት በተመሣሣይ የተቀናጀ ትምህርት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

4. ሆስፒታል ተኝተው መታከም ያለባቸው ተማሪዎች HHT ሊሰጥ የሚችለው –

a) ተማሪው(ዋ)HHT መስፈርት ማሟላት ከቻለ(ች)፣ እና

b) HHT በተገቢው ሁኔታ የተማሪዋ(ው)ን የህክምና እቅድ የሚደግፍ ከሆነ፣ እና በጤና ባለሙያው አስተያየት ተማሪው(ዋ) ትምህርት ለመቀበል የሚችል/የምትችል መሆኑ ከተረጋገጠ፥

c) አንድ ተማሪ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ውጭ በሆስፒታል ቆይቶ(ታ) ህክምና መከታተል አስፈላጊ ከሆነ፣ብቁ መምህር መኖሩ ሲረጋገጥ HHT ትምህርት እንዲሰጥ MCPS HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ መወሰን ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት MCPS-HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ፈቃድ ከሰጠ፣በሌላ አካባቢ የሚገኝ የትምህርት ኤጀንሲ የማስተማር አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

B. የወላጆች/የአሳዳጊዎች ኃላፊነት

1. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ተማሪዎች ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ህጋዊ መቅረትን (ማለትም ከ10 የትምህርት ቀናት በላይ) በተቻለ ፍጥነት ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ማሳወቅ እና ተማሪው(ዋ) የተጓደለውን የትምህርት ስራ የሚያካክስበትን/የምታካክስበትን ዕድል ለማመቻቸት ከተማሪው(ዋ) የትምህርት ቤት ካውንስለር ጋር መስራት አለባቸው።

2. የተማሪው(ዋ) የጤና ሁኔታ ከአራት ሳምንታት በላይ እንደሚቆይ የተማሪው(ዋ) የጤና ባለሙያ ከወሰነ(ች)፣ HHT ትምህርት እንዲሰጥ ለማመልከት ተማሪው(ዋ) ለአራት ሳምንታት ድረስ እስኪቀር መጠበቅ አስፈላጊም አይሆንም። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ ተማሪዎች በተቻለ ፍጥነት HHT እንዲጠይቁ ይበረታታሉ።

a) HHT ለማመልከት፣ የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ እና የተማሪው(ዋ) የጤና ባለሙያ– አለባቸው።

(1) MCPS ቅጽ 311-15B ወይም MCPS ቅጽ 311-15C መሙላት አለባቸው፣ እና

(2) ቅጹ በተቻለ ፍጥነት ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካውንስለር/ተወካይ መቅረብ አለበት።

b) የተማሪው(ዋ) የትምህርት ቤት ካውንስለር/ተወካይ ቅጾቹን ወደ HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

3. የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ MCPS ቅጽ 311-15B ወይም MCPS ቅጽ 311-15C በመፈረም MCPS ከተማሪው(ዋ) የጤና ባለሙያ ጋር እንዲነጋገሩ ፍቃድ ይሰጣሉ።

4. HHT መምህር እና የማስተማሪያ መርሃ ግብሩ እንደተዘጋጀ ወዲያውኑ የማስተማር አገልግሎቱ እንዲቀጥል ለማድረግ የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለባቸው።

a) HHT ጽ/ቤት አማካይነት ሌላ ሁኔታ ካልተመቻቸ በስተቀር፣ትምህርት የሚሰጠው ቨርቹዋል ነው።

b) HHT ትምህርት በሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ ኃላፊነት ያለው አዋቂ/ጎልማሳ ከተማሪው(ዋ) ጋር መሆን አለበ(ባ)ት።

c) HHTአስተዳዳሪ/ተወካይ ፍቃድ ሲሰጥ፣ሌሎች አዋቂ ሰዎች በሚገኙበት አካባቢ በሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ወይም ሌላ የሕዝብ አገልግሎት በሚሰጥበት ሕንፃ ውስጥ ለማስተማር ማመቻቸት ይቻላል። በዚህ ሁኔታ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ለመታዘብ ሌላ አዋቂ ሰው ላያስፈልግ ይችላል።

C. የትምህርት ቤት ካውንስለር ኃላፊነቶች

1. ተማሪው(ዋ) ለረዥም ጊዜ ከትምህርት ቤት የሚቀር/የምትቀር መሆኑ ከተረጋገጠ፤ተገቢው የአካዳሚክ ድጋፍ በጊዜ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ት/ቤቶች ወዲያውኑ ለትምህርት ቤት ካውንስለር/ተወካይ ማሳወቅ አለባቸው።

a) ከአራት ሳምንት ለሚያንስ ጊዜ ከትምህርት ቤት የመቅረት ሁኔታ ሲከሰት፤ የተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካውንስለር/ተወካይ ከተማሪው(ዋ)፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ከተማሪው(ዋ) አስተማሪዎች ጋር የቀረ(ች)በትን ጊዜ የአካዳሚክ ስራ የማካካስ እድሎች የሚፈጠሩበትን ሁኔታ ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

b) በአካላዊ ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ምክንያት ለአራት ሳምንታት ወይም ከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜ ከትምህርት ቤት የመቅረት ሁኔታ ሲያጋጥም፣የትምህርት ቤቱ ካውንስለር/ተወካይ HHT አገልግሎት ለማግኘት ማመልከት እንዳለባቸው ለቤተሰብ እና HHT ቢሮ ያማክራል/ታማክራለች።

2. የትምህርት ቤት ካውንስለር በወላጆች/አሳዳጊዎች/ተማሪዎች እና HHT ኬዝ ማናጀር መካከል እንደሚከተለው የአገናኝነት ሚና ይኖረዋል/ይኖራታል፡-

a) ቤተሰብ MCPS ቅጽ 311-15B ወይም MCPS ቅጽ 311-15C በቀጥታ ለት/ቤት ካውንስለር ያቀርባሉ፣ እና

b) HHT ኬዝ ማኔጀር ማንኛውንም የት/ቤት መረጃ እና ጉዳዮችን በተመለከተ ከትምህርት ቤቱ ካውንስለር ጋር ይመክራል፣እና HHT ማመልከቻ በመሙላት ሂደት ቤተሰብን ይረዳል/ትረዳለች።

3. የተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካውንስለር እና/ወይም የት/ቤት ቡድን ከወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ ተማሪ ጋር በመመካከር፣በአግባቡ ከጤና አገልግሎት ሰጪ የጤና ባለሙያ ሲፈቀድ፤ HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ 30 ቀናት ውስጥ ወደ ት/ቤት የመመለስ ሁኔታን የሚያረጋግጥ የመመለሻ እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው።

    a) ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ እቅድ ሲዘጋጅ ተማሪው(ዋ) በተቻለ ፍጥነት ወደ ትምህርት ቤት የመመለስን ሁኔታ ለመደገፍ ት/ቤቱ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ማድረግ የሚጠበቅባቸውን እርምጃዎች በመዘርዘር መገለጽ አለበት።

    b) HHT አገልግሎት የሚያስፈልግ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት የመመለሻ ዕቅድ ወደHHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።

4. ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ያለው/ያላት ተማሪ ከአራት ሳምንታት በላይ ከት/ቤት የሚያስቀር ሁኔታ መከሰቱን ወላጅ/አሳዳጊ ካሳወቁ በኋላ የትምህርት ቤቱ ካውንስለር/ተወካይ በተቻለ ፍጥነት ለ IEP ኬዝ ማኔጀር ወይም ለልዩ ትምህርት መምህር (RTSE) ማሳወቅ ይጠበቅበ(ባ)ታል።

    a) IEP ቡድኑ የተማሪ ከትምህርት ቤት የመቅረት ሁኔታ የሚጠበቅ መሆኑ በተገለጸ 10 ቀናት ውስጥ በመሰብሰብ ለተማሪው(ዋ) ድጋፍ ስለሚሰጥበት ሁኔታ እና በተማሪው(ዋ) IEP ፕሮግራም የሚያስፈልጉትን አገልግሎቶች የማቅረብ ሂደት ላይ መወሰን አለበት።

    b) በተጨማሪ ከዚህ በታች ያለውን ሰክሽን IV.F ይመልከቱ።

D. የተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ኃላፊነት

1. HHT አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው በተማሪነት ይቀጥላሉ።

2. ተማሪው(ዋ) ከ HHT መምህር ጋር እንደማይገናኙ HHT ለት/ቤቱ ካላሳወቀ በስተቀር ከትምህርት ቤት መቅረታቸው በ HHT ምክንያት መሆኑ ይመዘገብላቸዋል።

3. የትምህርት ክትትል ሪፖርትን በሚመለከት፤ተማሪዉ/ዋ ትምህርት ቤት ያልተገኘ(ች) ቢሆንም ከ MCPS የትምህርት አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት።

4. በትምህርት ቤት እና HHT የተቀናጀ አገልግሎት በማግኘት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች

5. HHT ትምህርት የሚያገኙት MCPS የትምህርት ካላንደር/የቀን መቁጠሪያ ጋር በተሳለጠ መልኩ ይሆናል።

6. HHT አገልግሎት ለሚሰጠው/ለሚሰጣት ተማሪ የተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ሁሉንም IEP ስብሰባዎች የማዘጋጀት እና የማካሄድ ሀላፊነት አለበት።

7. የተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት HHT አገልግሎት ለሚሰጠው/ለሚሰጣት ተማሪ መጽሃፍቶችን እና አስፈላጊ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ተገቢ አገልግሎቶችን ለምሳሌ፥ ስለ ኮሌጅ ምክር ወይም የኮርስ መመሪያዎችን መስጠት አለበት።

8. ለተማሪው(ዋ) HHT ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ውስጥ HHT በቅንጅት እና በተናጠል የትምህርት ስራዎችን ይሰጣል። HHT መምህራን የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የውጤት አሰጣጥ እና የሪፖርት አቀራረብ ፖሊሲዎችን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን እና መመሪያዎችን ይከተላሉ።

የክፍል አስተማሪዎች የተማሪን የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ ውጤት እና ተዛማጅ የኮርስ ክሬዲት ለመወሰን እንደአስፈላጊነቱ ከ HHS ለተማሪዋ(ው) የተሰጡ የትምህርት ስራዎችን ይጠቀማሉ። የኮርስ ክሬዲት ለመስጠት በኮርሱ ስራ ከተማሪው(ዋ) የሚጠበቀውን የትምህርት አፈጻጸም ግምገማ እና የትምህርት ችሎታ አፈጻጸም ግምገማዎችን በሚያረጋግጥ መልኩ መወሰን አለበት።

E. HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ኃላፊነቶች

1. HHT ማመልከቻ ከት/ቤቱ ካውንስለር ሲደርሰው/ሲደርሳት፣HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ በቤት እና በሆስፒታል ትምህርት ለመውሰድ የብቃት ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ፣የማስተማር ዘዴዎችን ለመቀየስ፣ እና እንደአስፈላጊነቱ HHT መምህር ለመመደብ እስከ 10 የትምህርት ቀናት ሊያስፈልግ ይችላል። HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ሪፈራሉ ከደረሰው/ከደረሳት በኋላ በፍጥነት የተማሪው(ዋ) ትምህርት እንዲቀጥል ለማድረግ የተቻለውን/የተቻላትን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለበ(ባ)ት።

2. HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ የማመልከቻውን ውጤት ለወላጅ/ለአሳዳጊ/ብቁ ለሆነ(ች) ተማሪ እና ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካውንስለር ያሳውቃል።

3. ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ፣HHTአስተዳዳሪው/ተወካዩ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ እቅድ መቼ ለHHT መቅረብ እንዳለበት ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካውንስለር ያሳውቃል።

4. HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ የማስተማር አገልግሎት የሚሰጥበትን ዘዴና ሁኔታ ይወስናል።

5. አግባብነት ያለው የማስተማር ዘዴ በተቻለ ፍጥነት ይጀመራል፣ነገር ግን HHT አስተዳዳሪው(ዋ) ተማሪው(ዋ) ወደ ትምህርት ቤት መምጣት አለመቻሉ(ሏ)ን እና የአገልግሎቱን አስፈላጊነት ከተረጋገጠ በኋላ ከ10 የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መጀመር አለበት።

6. ማሳወቂያው እና ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ HHT አገልግሎት ለመጀመር ለሌላ አራት ሳምንታት ማስተላለፍ አስፈላጊ አይሆንም። የብቁነት ሁኔታ ከተረጋገጠ እና የትምህርት አሰጣጥ ስልት ከተመቻቸ በኋላ አገልግሎት መስጠት ይጀመራል።

7. ሳምንታዊ የትምህርት ሰአት ብዛት የሚወሰነው የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት እና HHT አገልግሎቶችን የመቀበል ችሎታን በማመዛዘን ነው።

8. HHT ተፈቅዶላቸው በትርፍ ሰዓት በት/ቤታቸው መማር የሚችሉ ተማሪዎች በየሳምንቱ ቢያንስ ለሶስት ሰአታት HHT ትምህርት ይሰጣቸዋል፣ እንዲሁም HHT ተፈቅዶላቸው ነገር ግን በትምህርት ቤታቸው ተገኝተው መማር ለማይችሉ ተማሪዎች በየሳምንቱ ቢያንስ ስድስት ሰዓት HHT ትምህርት ይሰጣቸዋል።

9. ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጠው የትምህርት ክፍለጊዜ በተማሪው(ዋ) IEP ላይ በተገለፀው መሰረት በግል ለተማሪው(ዋ) አስፈላጊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፣ይኼውም የሚከናወነው ሰክሽን IV.G ላይ በተቀመጡት ዝቅተኛ መስፈርቶች እና የተማሪው(ዋ) HHT አገልግሎቶችን

የማግኘት ችሎታን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

10. ድንገተኛ ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ፣ የስርአተ ትምህርት እና የማስተማር ፕሮግራሞች ፅህፈት ቤት ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት (OCIP)/ተወካይ ለተማሪዎች HHT አገልግሎት እንዲሰጥ መፍቀድ ይችላል።

F. የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት

1. HHT ትምህርት የሚሰጣቸው ተማሪዎች MCPS ደንብ JEA-RA፣የተማሪ ትምህርት ላይ መገኘት ደንብ ላይ በተገለጸው መሰረት ከተፈቀደ ህጋዊ መቅረት በስተቀር በትምህርታቸው ላይ መገኘት አለባቸው።

   a) ወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ተማሪዎች HHT ተማሪው(ዋ) በታቀደው የትምህርት አገልግሎት የማይገኝ/የማትገኝ ከሆነ HHT ባለው መመሪያ መሰረት ለመምህሩ(ሯ) አስቀድመው ማሳወቅ አለባቸው።

   b) HHT መምህሩ(ሯ) ተማሪው(ዋ) በፍቃድ ለቀረ(ች)በት ጊዜ የማካካሻ መርሐግብር በማዘጋጀት ማስተማር ይችላል/ትችላለች። ጊዜው በማካካስ ከተጣጣ በተማሪው(ዋ) የውጤት መግለጫ ሪፖርት ቅጽ ላይ ቀርቷል/ቀርታለች ተብሎ አይመዘገብም።

   c) ህገወጥ ለሆነ መቅረት የማካካሻ ጊዜ አይሰጥም።

   d) HHT መምህሩ(ሯ) ከቀረ(ች) የትምህርት ጊዜውን መሟላት አለባቸው።

   e) ተከታታይ የሆነ ህገወጥ መቅረት ከትምህርት አገልግሎት መባረርን ሊያስከትል ይችላል።

G. ግላዊ የትምህርት ፕሮግራሞች (IEPs) ያላቸው ተማሪዎች

1. አንድ ተማሪ IEP ካለው/ካላት፣እና ተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት መሄድ ባለመቻሉ(ሏ) የሚከተሉትን አገልግሎቶች የማግኘት አስፈላጊነት ማረጋገጫ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማሳወቂያ በደረሰ 10 ቀናት ውስጥ የተማሪው(ዋ) IEP ቡድን መሰብሰብ አለበት –

   a) ስለ ተማሪው(ዋ)ን የትምህርት አገልግሎት የመቀበል ችሎታ ለመወያየት፣

   b) ተማሪው(ዋ) ትምህርት ማሻሻል ይችል/ትችል እንደሆነ ለመወሰን፣
   HHT ከማስተማር ጋር ትምህርት ማሻሻልን እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመስጠት ማናቸውንም አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር፣HHT ግቦችን ለመለየት እና ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት-ተኮር ፕሮግራም የመመለስ እቅድ ለማዘጋጀት፣ ወይም

   c) HHT ለተማሪው(ዋ) የትምህርት እድገት በቂ ካልሆነ የተማሪው(ዋ)ን IEP እና የምደባ ለውጥ ግምት ውስጥ በማስገባት

2. IEP ቡድን IEP ቅጂውን ወደHHT ያስተላልፋል።

3. እንዲሁም HHT ሲቋረጥ እና ተማሪው(ዋ) ወደ ትምህርት ቤቱ(ቷ)

በሚመለስበት/በምትመለስበት ጊዜ IEP ስብሰባ መደረግ አለበት።

4. IEP ያለው/ያላት ተማሪ በስሜታዊ የጤና እክል ምክንያት HHT ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል ተብሎ ከተወሰነ HHT የሚሰጠው የማስተማር አገልግሎት ከ 60 ተከታታይ የትምህርት ቀናት መብለጥ የለበትም።

5. – በመጠባበቅ ላይ ለሚገኝ/ለምትገኝ የአካል ጉዳተኛ ተማሪ HHT እንደ ጊዜያዊ ምደባ ሊሆን አይችልም።

   a) ህዝባዊ ባልሆነ ልዩ ት/ቤት ምደባ፣ ወይም

   b) ሌላ ማንኛውም የምደባ ለውጥ እስከሚደረግ

H. ቀጣይ አገልግሎት የማግኘት ብቃት

1. HHT አገልግሎቶችን ለማግኘት የተማሪው(ዋ)ን ብቁ አካላዊ ወይም ስሜታዊ የጤና እክል ሁኔታ በየጊዜው እንደገና መገምገም ይጠይቃል —

   a) ከመጀመሪያው የብቃት ማረጋገጫ በኋላ 60 የትምህርት ቀናት እና ከዚያ በኋላ በእያንዳንዱ 60 የትምህርት ቀናት፤ ወይም

   b) ከዚያ በፈጠነ ጊዜ ውስጥ፣በወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ወይም ከ MCPS በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት

2. የአገልግሎት መመዘኛዎችየተቀናጀ የትምህርት አገልግሎት ለሚሰጣቸው ተማሪዎች በየዓመቱ እንደገና መረጋገጥ አለበት።

I. HHT መምህራን

1. HHT መምህር የኮንትራት ውል በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መካከል በሚደረገው ድርድር ውስጥ ይካተታል።

2. የሰው ሃብት እና ልማት ጽ/ቤት በየጊዜው ብቁ የሆኑ HHT መምህራንን ዝርዝር ወደHHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ያስተላልፋል። HHT እጩ አስተማሪዎች HHT አስተዳዳሪ/ተወካዩ ቃለ መጠይቅ ያደርግላቸዋል፣እና ቅጥር ከመከናወኑ በፊት HHT መግለጫ በሚሰጥበት ፕሮግራም ላይ ይሳተፋሉ።

3. HHT አስተማሪዎች HHT ተማሪዎችን በማንኛውም ጊዜ ማጓጓዝ የለባቸውም።

4. HHT አስተማሪዎች ለሚከተሉት የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች ተገዢ ናቸው፡-

   a) HHT አስተማሪዎች MCPS ደንብ JHC-RA መሠረት የህፃናት ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራን በተመለከተ የተጠረጠረ ወይም የተስተዋሉ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለህጻናት ጥበቃ አገልግሎት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

   b) ተማሪው(ዋ) አደንዛዥ ዕፅ ይወስዳል/ትወስዳለች ተብሎ የተጠረጠረ ወይም የታየ ሁኔታ ካለ በአግባቡ ለወላጅ/ለአሳዳጊ እና HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ሪፖርት መደረግ

አለበት፥ (MCPS ደንብ IGO-RA፣ተማሪዎችን የሚመለከት የአልኮል፣ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ መጠቀም ስለሚያስከትለው ተፅእኖ መመሪያውን ይመልከቱ)።

c) ማንኛውም ራስን የመግደል አዝማሚያ MCPS ቅጽ 335-54ራስን የመግደል ስጋት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽላይ የተቀመጡትን ደረጃዎች በመከተል አስቸኳይ መፍትሔ መሰጠት አለበት። ለድንገተኛ አደጋ ህክምና 911 መደወል ያስፈልጋል፣ በመቀጠልም ለተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ እና HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ ማሳወቅ ያስፈልጋል። ሕክምና የማያስፈልገው ድንገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታን በሚመለከት፣HHT መምህር MCPS ቅጽ 335-54 ላይ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ይከተላል።

5. MCPS ቅጽ 311-13፣ በየሁለት ሣምንቱ ከመምህራን የሚቀርብ መካከለኛ/ጊዜያዊ የማስተማር አገልግሎት ሪፖርት፣ከእያንዳንዱ የማስተማር ክፍለጊዜ በኋላ (በህዝብ መገልገያ ስፍራ ላይ ስብሰባ ተደርጎ ከሆነ) የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥበትን ጊዜ ለማረጋገጥ ጎልማሳ/አዋቂ ሰው በታዛቢነት ወይም በተማሪው(ዋ) ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል።

6. HHT አስተማሪዎች እንደአግባቡ HHT አስተዳዳሪ/ተወካይ እና/ወይም ከተማሪው(ዋ) የትምህርት ቤት ካውንስለር ጋር በመመካከር የተማሪን መረጃ ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው።

## V. *ግምገማና ክለሳ*

HHT አተገባበር ላይ የሚነሱ አለመግባባቶች HHT አስተዳዳሪ/ተወካዩ ሊፈቱት የማይችሉ ከሆነ፣መፍትሄ ለማግኘት ወደ ተባባሪ ሱፐር ኢንተንደንት OCIP/ተወካይ ይቀርባሉ። ተባባሪ ሱፐር ኢንተንደንት OCIP/ተወካይ እንደ አስፈላጊነቱ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ይመክራል።

***ተዛማጅ ምንጮች፦*** የተብራራ የሜሪላንድ የትምህርት ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ ሰክሽን 7-301.1፣የሜሪላንድ የተብራራ ህግ ኮድ፣ §13A.03.05.01-.05፣ እና §13A.05.01.10.C(5)

***የደንቡ ታሪክ፦*** ሜይ 10,1990 አዲስ ደንብ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ ጁላይ 1 ቀን 1995 ተሻሽሏል።ሴፕቴምበር 21 ቀን 2006 ተሻሽሏል፣ኖቬምበር 6 ቀን 2009 ተሻሽሏል፣ጁላይ 18 ቀን 2011 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ጁን 28, 2016 ተሻሽሏል፣ዲሴምበር 13, 2016 መጠነኛ ክለሳ ተደርጎበታ፣ጁን 13, 2018 ተሻሽሏል፣ጃኑዋሪ 26, 2024 ተሻሽሏል፣ሴፕቴምበር 4, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድኢንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024